# 8ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በአል ኅዳር 29 ቀን 2006 ዓ.ም. በሮም ከተማ በድምቀት ተከበረ

8ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በአል በሮም ከተማ ኅዳር 29 ቀን 2006 ዓ.ም. በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ በአሉ በሮም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲና በሮምና አካባቢዋ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ሲሆን፤ በበአሉ ከ250 በላይ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተዋል፡፡ በበአሉ መክፈቻ ለቀድሞው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ/ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊና በትግሉ ለተሰው ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት ተደርጓል፡፡




በመቀጠልም ፌዴራሊዝምና የዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባታ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት እንዲሁም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥትና የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ ተጠቃሚነት በሚሉ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ አወያይነት አንድ የዳያስፖራና አንድ የሚሲዮኑ አባል ለተሳታፊዎች ሰፊ ገለጻ ያደረጉ ሲሆን፤ በርዕሶቹ ዙሪያ ከተሰብሳቢዎች አስተያየቶችና ጥያቄዎች ቀርበው ውይይት ተደርጐባቸዋል፡፡

በዚሁ ፕሮግራም እለቱን በማስመልከት የተዘጋጀው ዳቦ የመቁረስና ሻማ የማብራት ሥነ-ሥርዓት በብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች በጋራ የተከናወነ ሲሆን በአንድ ወጣት የተዘጋጀ ግጥም ተነቧል:: በተጨማሪም በሮም የሚኖሩ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ተወላጆች የሶማሌ ብሔረሰብ ባህላዊ ልብሶችን በመልበስ የሶማሌኛ ዘፈኖችን ለታዳሚዎች አቅርበዋል::






ከዚህ ሌላ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰንደቅ ዓላማና የዘጠኙ የፌዴራል ክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች የየክልሎቹን ባህላዊ አልባሳት በለበሱ ወጣቶች በተሣታፊዎች ፊት እየተውለበለቡ እንዲያልፉ የተደረገ ሲሆን፤ ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል ቦንድ ለገዙ የሮም ከተማ ነዋሪዎች የተዘጋጀው የምሥክር ወረቀት በክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ ተሰጥቷል:: በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ መዝሙር በጋራ ተዘምሮ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል::



